በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ለፍትሕ ሚኒስቴር
አዲስ አበባ

# የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ረቂቅ አዋጅ ላይ ከተማለከቱት ድንጋጌዎች ወስጥ አስተያየት ቢቀርብባቸው በማግስት እንደገና ሊታዩና ሊለወጡ ይችላሉ ተብለው በታመባቸው የረቂቁ ክፍሎች ላይ በሲቪል ማህበራት ተወካዮች የቀረበ አማራጭ ሃሳብ

ሰኔ 8 ቀን 2000 ዓ.ም.

## መግቢያ

እንደሚታወቀው መንግሥት በፌደራል ደረጃ የሚሰሩ የበጐ አድራጐት ድርጅቶች እና ማሕበራትን ለማስተዳደር የሚያስችል ህግ በማርቀቅ ሂደት ላይ ነው፡፡ ምንም እንኳን የማርቀቅ ሂደቱ ከተጀመረ ዓመታት ያስቆጠረ ቢሆንም አሁን ለውይይት የቀረበው ረቂቅ ህግ በመንግሥት ለህዝብ ውይይት ከቀረበ ሁለት ወር አይሞላውም፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ የረቂቅ ህጉን ለማዳበር እና ግንዛቤ ለማስጨበጥ በመንግሥት በኩል የተለያዩ ለወደፊቱም ሊበረታቱ የሚገባቸው ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ በዚህ ረገድ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከዘርፉ ማኅበረሰብ ጋር ያደረጉትን ሰፊ ውይይት ለማድነቅና ለማመስገን እንወዳለን፡፡

ይህ ጽሁፍ የቀረበው ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከዘርፉ ማኅበረሰብ ጋር በአደረጉት ውይይት በረቂቅ ህጉ ላይ የሚቀርቡ ዝርዝር አማራጮች ካሉ መቅረብ እንደሚችሉ ነገርግን እነዚህ የሚቀርቡ አማራጮች መንግሥት የማይለወጥ አቋም የወሰደባቸውን ጉዳዮች ሊማለከቱ እንደማይገባ ባሳሰቡት ማሰረት ነው፡፡ በመሆኑም ምንም እንኳን ለዘርፉ ህልውናና ማጠናከር እጅግ ወሳኝ ቢሆኑም በረቂቅ ህጉ ላይ የበጐ አድራጐት ድርጅቶችን እና ማሕበራትን በሚመለከት የተሰጡትን የምንነት ትርጉሞች፤ የገቢ ምንጭ፤ በተወሰኑ የሥራ ዘርፎች ውስጥ የመሳተፍ እና ፍርድ ቤት የመቅረብ መብቶች ላይ አማራጭ ሃሳቦችን አላቀረብንም፡፡

ጽሁፉ በረቂቅ ህጉ በእንዳንዱ አንቀጽ ሥር ላይ መብራራት ያለባቸው ድንጋጌዎች እንዲብራሩ፤ ማሰረዝ ያለባቸው እንዲሰረዙ እና አዲስ መጨመር ያለባቸው  ነጥቦች ደግሞ እንዲጨመሩ ተደርጎ ተዘጋጅቷል፡፡ ይህን አማራጭ በማዘጋጀቱ ረገድ የዘርፉ ማህበረሰብ ውይይት እጅግ ወሳኝ መሆኑን ብንረዳም አማራጩን ለማቅረብ ከተሰጠን በጣም አጭር ጊዜ አንጻር ሰፊ እና ጥልቅ ውይይት ማድረግ አልተቻለም፡፡ እንዲሁም የጊዜው እጥረት አማራጩን በጥልቅ ጥናትና የሌሎች አገሮችን ተሞክሮ ላይ ማሰረት አድርጎ ለማቅረብ የነበረው ሃሳብም አልተሳካም፡፡

በመጨረሻም ምንም እንኳን ከላይ የተማለከቱት ችግሮች ቢኖሩም የቀረቡት አማራጮች በረቂቅ ህጉ ላይ የዘርፉ ማህበረሰብ ያነሷቸውን ጥያቄዎች በተወሰነ ደረጃ ሊመልሱ ሥለሚችሉ የህጉ መንግስትና የህጉ አርቃቂዎች አማራጮቹን ከግምት ውስጥ በማስገባት ረቂቁን እንዲያሻሽሉት በሲቪል ማህበረሰቡ ሥም በማክበር እንጠይቃለን፡፡

Members of the Taskforce

ሰኔ 9 ቀን 2000 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# <u>የበጐ አድራጎት ድርጅቶች እና የማሕበራት ረቂቅ አዋጅ ቁ.00/2000</u>

በሕገ መንግሥቱ የተረጋገጠውን የዜጎችን <u>ለማንኛውም ሕጋዊ ዓላማ</u> የመደራጀት መብት ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ሕግ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የበጐ አድራጎት ድርጅቶችን እና ማሕበራትን <u>ነፃነት እና ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ</u> የበጐ አድራጎት ድርጅቶችንና ማሕበራትን መመዝገብ፣ ፈቃድ ማስጠት እና መቆጣጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የበጐ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት በኢትዮጵያ ሕዝቦች ሁለንተናዊ እድገት ውስጥ ያላቸውን ሚና <u>እና አጋርነት</u> ለመደገፍና ለማሳለጥ የተሟላ የሕግ ማዕቀፍ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55/1/ መሠረት የሚከተለው ታወጇል፡፡

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

**1. አጭር ርእስ**

ሀ. የለም

**2. ትርጉም**

**ተጨማሪ፡-** <<የውጭ ገንዘብ ማለት>> ከውጭ አገር መንግሥታት፣ ኢምባሲዎች እና የውጭ አገር ዜጎች ድርጅቶች የሚገኝን ገንዘብ ብቻ ነው፡፡ ሆኖም የኢትዮጵያ መንግሥት በፈረመው አለም አቀፍ ሥምምነት መሰረት ለበጐ አድራጎት ድርጅቶችና ማሕበራት ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚደረግ ድጋፍን አይጨምርም፡፡

ንኡስ ቁጥር 8 ንኡስ ቁጥር 14 ቢሆን

**3. የተፈጻሚነት ወሰን**

1. ይህ ሕግ በሚከተሉት የበጐ አድራጎት ድርጅቶችና ማሕበራት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**ተጨማሪ፡-** የአገር አቀፍ **ባህርይ ባላቸው ጉዳዮች ላይ** በ**ሚሰሩ**

2. ይህ ሕግ ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ጋር በሚደረግ ስምምነት መሠረት በኢትዮጵያ ወስጥ በሚንቀሳቀሱ ዓለም አቀፍ ወይም አህጉራዊ ወይም ክፍለ አህጉራዊ ወይም የውጭ ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረወም፡፡

**ተጨማሪ፡-** ይህ ሕግ በሃይማኖት ተቋማት ላይ ተፈፃሚነት የለወም፡፡

**ተጨማሪ፡-** በልዩ ባሕርያቸው ምክንያት በሌላ ሕግ የሚሸፈኑ ማህበራት በዚህ አዋጅ አይገዙም፣

**ተጨማሪ፡-** ሚኒስትሩና የሚመለከተው የዘርፍ አስተዳዳሪ ሚኒስትር በልዩ ሁኔታ የውጭ ዜጎች በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ማህበር እንዲመሠርቱ ወይም በውጭ ሃገር ህግ መሰረት የተቋቋመ ማህበር በዚህ ህግ መሰረት እንዲመዘገብ ሊፈቅዱ ይችላሉ፡፡

ክፍል ሁለት
ስለበጐ አድራጎት ድርጅቶችና ማሕበራት ኤጀንሲ መቋቋም

**4. መቋቋም**

ሀ. የለም

**5. የኤጀንሲው አላማዎች**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

**ተጨማሪ፡-** የበጐ አድራጎት ድርጅቶችና ማሕበራት እራሳቸወን በራሳቸው እንዲቆጣጠሩ ማበረታታት እንዲሁም አቅማቸወን በተሟላ መልኩ ማጠቀም እንዲችሉ ተገቢወን ድጋፍ ማድረግ ናቸው፡፡

**6. የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባራት**

1. ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

ሀ. በዚህ ሕግ መሠረት ለበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማሕበራት መመዝገብ፤ የሥራ ፈቃድ ማስጠት፣ ማደስ እና እና መቆጣጠር

2. አ. የለም

**7. የኤጀንሲው አደረጃጀት**

አ. የለም

**8. የኤጀንሲው ዳይሬክተርና ምክትል ዳይሬክተር አሿሿም**

አ. የለም

**9. የዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር**

አ. የለም

**10. የምክትል ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር**

1. አ. የለም

**11. የኤጀንሲው ሬጅስትራር አሿሿም**

አ. የለም

**12. የሬጂስትራሩ ሥልጣንና ተግባር**

አ. የለም

**13. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማሕበራት ምክር ቤት፣**

1. የዘርፍ አስተዳዳሪዎችን ፣ ሌሎች በሚኒስትሩ የሚመደቡ የመንግሥት አካላትን እና የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማሕበራት የሚመርጧቸው ተወካዮችን በአባልነት ያቀፈ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማሕበራት ምክር ቤት ይቋቋማል፡፡

2. አ. የለም

**ተጨማሪ፡-** በምክር ቤቱ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና የማሕበራት ተወካዮች ብዛት ከምክር ቤቱ አባላት ጠቅላላ ቁጥር ከ50% አያንስም፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተጠቀሰው ቢኖርም እንደአስፈላጊነቱ በኤጀንሲው አቅራቢነት ሚኒስትሩ ለማህበረሰብ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረከቱ እና በዘርፉ ጥልቅ እውቀት ያላቸው ኀብረተሰቡን የሚወክሉ ከሁለት የማይበልጡ ሰዎችን የምክር ቤቱ አባል አድርጎ ሊመድብ ይችላል፡፡

**14. የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግበር**

1. ምክር ቤቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፣

   ሐ. በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማሕበራት ዘንድ የራስ አስተዳደርን (Self Regulation) በማበረታታት የሚልከም አስተዳደር መርሕ እንዲኖር ጥረት ያደርጋል፣

**ተጨማሪ፡-** ከበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ከማህበራት ሥራዎች ሕብረተሰቡ የላቀ ተጠቃሚ መሆኑን ለማረጋገጥ ኤጀንሲው ሊከተላቸው የሚገቡ መስፈርቶችን እና ደረጃዎችን (benchmarks and standards) ያወጣል፡፡

   ረ. የማህበራትና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች አስተዳደር የበላይ አካል ሆኖ ይሰራል፤

**ተጨማሪ፡-** ኤጀንሲው እና ሚኒስትሩ በዚህ ሕግ ቁጥር 73፣ 74፣79 ፣86 ፣94 ፣104 እና 105 መሰረት በሰጧቸው ወሳኔዎች ላይ ቅሬታ ይቀበላል ፡፡ይግባኝ ይሰማል ፣ ወሳኔወን ያፀናል፣ያሻሽላል ወይም ወድቅ ያደርጋል፤

**ተጨማሪ፡-** ምክር ቤቱ በይግባኝ በሚመለከታቸው የኤጀንሲው ወሳኔዎች ላይ የኤጀንሲው ዳይሬክተር በአስረጂነት ካልተጠየቀ በቀር ሊሳተፍ አይችልም፡፡ ሆኖም የኤጀንሲው ሬጅስተራር ዳይሬክተሩን ተክቶ በጸሃፊነት ምክር ቤቱን ያገለግላል

2. ምክር ቤቱ የሚያከናወናቸወን ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራት ሊወስን ይችላል፡፡

**15. የምክር ቤቱ ስብሰባ**

   አ. የለም

**የዘርፍ አስተዳዳሪዎች ሥልጣንና ተግባር (አንቀጽ 71 የነበረው እዚህ ቢመጣ)**

1. በፈቃድና ምዝገባ ሂደት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማህበራትን ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሚገመግሙ አስተያየት የሚሰጡ ባለሙያዎችን በቋሚነት በኤጀንሲው ጽ/ቤት ይመድባል፡፡
2. በማቋቋሚያ ሕጉ በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሠረት የሥራ እንቅስቃሴዎቸወን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ሙያዊ ምክር ይሰጣል የገቡበትን ኃላፊነት በማይወጡት ላይ አስፈላጊወን እርምጃ እንዲወሰድ ለኤጀንሲው ሃሳብ ያቀርባል፡፡
3. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችንና የዘርፍ አስተዳዳሪወን የጋራ ግቦች ለማሳካት የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ተቀናጅተው የሚሰሩበትን ሁኔታ ያመቻቻል (አንቀጽ 99 እዚህ ቢመጣ)

**የዘርፍ አስተዳዳሪዎች (አንቀጽ 72 የነበረውእዚህ ቢመጣ)**

አ የለም

ክፍል ሶስት

የበጐ አድራጐት ድርጅቶች

**ንዑስ ክፍል 1. አጠቃላይ**

**16. ትርጉም (አንቀጽ 16 የነበረው)**

3.

የዜግነትን ማራመድ **(የቦታ ለውጥ)**

ማሕበረሰባዊ እድገትን ማራመድ፣ **(የቦታ ለውጥ)**

**ተጨማሪ**፡- የአርብቶ አደሩን ሕይወት የሚለወጡ ፕረቶችን ማስፋፋት

**ተጨማሪ**፡- በተለያዩ ማስኮች ምርምርና ጥናት ማድረግ፤ የወይይት መድረኮችን ማዘጋጀት እና መረጃን ማሰራጨት

**17. የበጐ አድራጐት ድርጅቶች**

1. የበጐ አድራጐት ድርጅት፣
2. በማናቸውም ዓይነት የተቋቋሙ የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ሕጋዊ ሰውነት ለማግኘት መመዝገብ አለባቸው፡፡

**ተጨማሪ፡-** ሕጋዊ ሰውነት በሌላቸው የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ወስጥ የሚገኙ አባላት ወይም ሠራተኞች ድርጅቶቹ ለሚያደርሱት ማንኛውም ዓይነት ጥፋት ወይም ጉዳት በአንድነትና በነጠላ ሃላፊዎች ይሆናሉ

3. የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ሥራቸውን የሚያስተባብር እና በጋራ የቆሙትን ዓላማ ለማስካት የሚችላቸው ህጋዊ ሰውነት ያለው የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ሕብረት ማቋቋም ይችላሉ፡፡
4. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ እንደተጠበቀ ሆኖ የበጐ አድራጐት ኩሜቴዎች በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ይገዛሉ፡፡

**ከአንቀጽ 18 እስከ 59 ባሉት ላይ የቀረበ አስተያየት የለም**

ክፍል አራት

ማህበራት

**60. ትርጉም**

1. በዚህ አዋጅ መሰረት “ማህበር” ማለት ለትርፍ ሳይሆን ለሌላ ማንኛውም ሕጋዊ ዓላማዎች የተቋቋመ ቁጥራቸው ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች ስብስብ ሆኖ ሕዝባዊ፣ የብዙሃን ወይም የሙያ ማህበራት የሚያካትት ነው፡፡
2. ማህበራት ሥራቸውን የሚያስተባብር እና በጋራ የቆሙለትን ዓላማ ለማሳካት የሚችሉበት ህጋዊ ሰውነት ያለው የማህበራት ሕብረት ሊቋቋም ይችላሉ፡፡

**61. የማሕበራት ሕጋዊ ሰውነት**

ሀ. የለም

**62. የማህበራት መብቶችና ግዴታዎች**

1. ማንኛውም ማህበር አባላትን የሚቀበለውና የሚያሰናብተው በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ነው፡፡ **(የቦታ ለውጥ ን. አ. 4 የነበረው)**

**6 ቢሰረዝ**

7. ኢትዮጵያውያን ማህበራት በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እና በምርጫ ሂደት በተለይም ትምህርታዊ ሴሚናሮችን በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በማዘጋጀት፣ የተወዳዳሪዎችን ፕሮግራም በሚዲያት፣ የምርጫ ሂደቶችን በመታዘብ እና ከምርጫ አስፈጻሚ አካላት ጋር በመተባበር ረገድ በንቃት መሳተፍ ይችላሉ፡፡

**63. የማሕበራት አደረጃጀት**

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ቢኖርም ማንኛውም ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ፣ የሥራ አስፈጻሚ ወይም ቦርድ እና ኦዲተር የያዘ መሆን አለበት፡፡

**4. ቢሰረዝ**

**64. የጠቅላላ ጉባኤው ሥልጣንና ተግባራት**

1. በሕግና በማሕበሩ መተዳደሪያ ደንቦች መሠረት ጠቅላላ ጉባኤው የማህበሩ የበላይእና የመጨረሻ አካል ሆኖ፣

**ተጨማሪ**፡- የማህበሩን ሥራ አስፈፃሚ (ቦርድ) አባላትን ይመርጣል፤ያግዳል ያሰናብታል

**ተጨማሪ**፡- የቦርዱን ሥልጣንና ተግባር ይወስናል፤ ሥራውንም ይቆጣጠራል

ለ. በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት የማሕበሩን ኦዲተር ይመርጣል፣ ያሰናብታል፣ የከፍያውንም ጣሪያ ይወስናል፡፡

ሐ. የማህበሩን ቅርንጫፎች ማከፈትና ማዘጋት እንዲሁም የማሕበሩን መፍረስ ይወስናል፤

**65. ከጠቅላላ ጉባኤው ውሣኔዎች ማየት**

**2. ቢሰረዝ**

**66. የጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባዎች**

**ተጨማሪ፡-** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ሰብሳቢው በቂ ባልሆነ ምክንያት በ30 ቀናት ወስጥ ስብሰባ ያልጠራ ከሆነና ለመጥራትም ፍቃደኛ ካልሆነ 1/3ኛ የሚሆኑት አባለት ለኤጀንሲው በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት ሥብሰባወን እንዲጠራ ወይም ያልጠራበትን ምክንያት እንዲያስረዳ ኤጀንሲው የማህበሩን ሰብሳቢ ሊጠይቀው ይችላል፡፡

**ተጨማሪ፡-** ኤጀንሲው ሥበሰባው ያልተጠራበትን ምክንያት መርምሮ ሥብሰባወን ላለመጥራት በሰብሳቢው የቀረበው ምክንያት በቂ ሆኖ ካላገኘው በ 30 ቀናት ወስጥ ሥበሰባወን እንዲጠራ ሊያዘው ይችላል፡፡

**ተጨማሪ፡-** ሰብሳቢው በኤጀንሲው በተሰጠው ትዕዛዝ ማሰረት ሥበሰባወን ባይጠራ በኤጀንሲው አማካይነት የጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡
የጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ የተጠራው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /4/ መሠረት ከሆነ የዕለቱን ስብሰባ ለማምራት ሊቀመንበር የሚሆን ሰው አባላቱ እንዲመርጡ ኤጀንሲው ያደርጋል፡፡

የጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ ስብሰባ ለመጥራት ሁሉም ሊያወቀው የሚችል ማስታወቂያ ማውጣት አለበት፡፡

የማህበሩ ምልዐተ ጉባኤ የወከልና ተሳትፎን ሥርዓት ጨምሮ በመተዳደሪያ ደንቡ በተወሰነው መሠረት ይሆናል፡፡ ይህን የሚሟከት ድንጋጌ በሌለበት ሁኔታ የስብሰባው አብዛኛው አባላት ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይኖራል፡፡ ሆኖም መተዳደሪያ ደንቡ ከማህበሩ አባላት ከ50% በታች ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይኖራል ብሎ መደንገግ አይችልም፡፡ ለሁለት ተከታታይ ስብሰባዎች ምልዓተ ጉባዔ ካልተሟላ በሚቀጥለው ሦስተኛ ስብሰባ ከአባላቱ 50% ባይገኙም ምልዓት ጉባዔ እንደተሟላ ይቆጠራል፡፡

የዚህ ድንጋጌ ቁጥር 7 ቢሰረዝ

**67. የውጭ ኦዲተር ሥልጣንና ተግባራት**

1. የውጭ ኦዲተሩ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤው ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

ለ. በኢትዮጵያ ወስጥ ተቀባይነትን ባገኙ መመዘኛዎች መሠረት የድርጅቱን የኦዲት ሪፖርት ያዘጋጃል፡፡ ለጠቅላላ ጉባኤው አቅርቦ ያፀድቃል፡፡

**68. አባላትን የሚመለከቱ መረጃዎች**

1. የማሕበሩ የሥራ መሪዎች የአባላቱን ማንነትና አድራሻ ይመዘግባሉ፣ ይጠብቃሉ፣ ሲጠየቁ ለኤጀንሲው ያቀርባሉ፡፡
2. ቢሰረዝ
3. የአባላቱ ቁጥር ከሁለት በታች ሲወርድ እና አዲስ አባላትን መተካት ካልተቻለ ቀሪው አባል ጉዳዩን ለኤጀንሲው ያቀርባል፡፡
4. ቢሰረዝ
5. ቢሰረዝ

## ክፍል አምስት

## የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማሕበራት አመሠራረት፣ ፈቃድ አሰጣጥና ምዝገባ

**ንዑስ ክፍል 1 የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማሕበራት አጣራረት**

**69. አማሰራረት**

1. የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማሕበራት በዚህ ሕግ የተቀመጠውን አነስተኛ የመስራች አባላት ቁጥር አሟልተው ሲገኙ እንደተመሠረቱ ይቆጠራል፡፡

**ተጨማሪ፡-** ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማሕበር ህጋዊ ሰውነት እና የሥራ ፍቃድ ሰርተፊኬት ለማግኘት ከፈለገ ለምዝገባ ማመልከት አለበት፡፡

**2. ቢሰረዝ**

**70. የመመስረት ወጪ**

1. ሀ. የለም
2. ሀ. የለም
3. ተጨማሪ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበራት ከመመዝገባቸው በፊት የሚያሰባስቡት ገንዘብ ወይም ንብረት ከብር መቶ ሺ በላይ ከሆነ መሥራቾቹ የተሰበሰበውን ገንዘብ

ማጠን እና የተደረጉ ወጪዎችን ለኤጀንሲው ማሳወቅ አለባቸው፡፡ ኤጀንሲው እነዚህን ማህበራት እንዲማዘገቡ ሊያስገድዳቸው ይችላል፡፡

4. አ. የለም

5. አ. የለም

**ተጨማሪ፡-** ከላይ በተማለከቱት ምክንያቶች ባለመመዝገቡ ምሥረታው የተቋረጠ ማህበር በምሥረታው ሂደት ከአባላት መዋጮ ሌላ ያሰባሰበው ገንዘብ ካለ ተመሳሳይ ዓላማ ላላቸው ወይም ለሌሎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እንዲተላለፍ ኤጀንሲው በፍርድ ቤት ሊያስወስን ይችላል፡፡

**ንዑስ ክፍል 2 የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማሕበራት ምዝገባ**

**71. አንቀጽ 16 ቢሆን**

**72. አንቀጽ 17 ቢሆን**

**73. ምዝገባ**

1. <u>በዚህ አዋጅ አንቀጽ 74 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኤጀንሲው ማመልከቻ ሲቀርብለት በዚህ አዋጅ የተደነገጉት አስፈላጊ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ካረጋገጠ በኋላ አመልካቾቹን በበጎ አድራጎት ድርጅትነት ወይም በማሕበርነት በመመዝገብ የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡</u>
2. ማንኛውም ለምዝገባ የሚቀርብ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ከዚህ የሚከተሉትን አሟልቶ በቀረበ ጊዜ ኤጀንሲው <u>ከ ሰላሳ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ወስጥ</u> አመልካቹን በመመዝገብ የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ ይሰጣል ወይም ምዝገባው ተቀባይነት ያለማግኘቱን በጽሁፍ ይገልፃል፡፡
    - ከሀ እስከ ሠ ባሉት ላይ አ. የለም
    - ረ. ቢሰረዝ
3. አ. የለም

**ተጨማሪ፡-** ከላይ በንዑሥ አንቀጽ 2 በተጠቀሰው ጊዜ ወስጥ ኤጀንሲው ለአመልካቹ ወሳኔውን ካላሳወቀ አመልካቹ እንደተመዘገበ ይቆጠራል

4. አ. የለም፡፡
5. አ. የለም፡፡

**74. የምዝገባ ጥያቄን ስላለመቀበል**

1. ኤጀንሲው ከሚከተሉት አንዱ ምክንያት መኖሩን ካረጋገጠ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም ማሕበሩን አይመዘግብም፡፡

ሀ. ሊቋቋም የታሰበው የበጐ አድርጎት ድርጅት ወይም ማህበር መተዳደሪያ ደንብ የድርጅቱን ወይም የማህበሩን የሥልጣን መዋቅር በግልጽ የማያመለክት፣ ለመመራትና መቆጣጠር የማይስችል ከሆነ

ለ. ሊቋቋም የታሰበው የበጐ አድራጎት ድርጅት ወይም ማሕበር ሕገ-ወጥ ለሆነ፣ የሕዝብን ሠላም ለሚያደፈርስ ወይም የኢትዮጵያን ደህንነት እና ሚረጋጋት ለመጉዳት ማጠቀሚያ ሊሆን ይችላል የሚያሰኝ ተጨባጭ ማስረጃ ሲኖር፣

ሐ. ቢሰረዝ

መ. የምዝገባ ማመልከቻው የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የማያሟላ ሲሆን፣

ሠ. ቢሰረዝ

2. ወደ አንቀጽ 3 (5) ቢካተት፡፡

3. ኤጀንሲው ከሚከተሉት በአንዱ ምክንያት ምዝገባ ሊከለክል ይችላል፣

ሀ. የበጐ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 105 /ለ/ /ሐ/ /መ/ /ቀ/ ላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ቀደም ሲል የፈረሰ ከሆነ፣

ለ. የበጐ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማሕበሩ የሥራ መሪዎች እነማን መሆን እንዳለባቸው ወይም ንብረቶቹን የመያዝ ወይም የማስተዳደር ሥልጣን በተመለከተ በአባላት መካከል ስምምነት የሌለ እንደሆነ እና ምዝገባወን በመቃወም ሊመሰረት የታቀደው የበጐ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማሕበሩ አብላጫ መስራች አባላት ለኤጀንሲው ካመለከቱ፣ ወይም

ሐ. ቢሰረዝ፣

መ. አ. የለም

ሠ. ቢሰረዝ፣

ረ. ቢሰረዝ፣

4. አ. የለም፡፡

**ተጨማሪ -** ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ መሰረት ተሟልተው ያልቀረቡ የምዝገባ ጥያቄዎች ሲቀርቡለት ምዝገባወን ሙሉ በሙሉ ከመከልከሉ በፊት ትክክል አይደለም የተባለው ጉዳይ እንዲስተካከል እና የጎደለ ማስረጃ ካለ ተሟልቶ እንዲቀርብ አመልካቹን ማስረዳትና እድል መስጠት አለበት፡፡

**75. በሥራ መሪነት መሥራት የማይችሉ ሰዎች**

አ. የለም

**76. የበጐ አድራጎት ድርጅቶችና ማሕበራት መዝገብ**

አ. የለም

**77. የበጐ አድራጎት ድርጅት ወይም ማሕበር ቅርንጫፍ**

1. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የከፈተውን ቅርንጫፍ በሦስት ወር ጊዜ ወስጥ ለኤጀንሲው ማሳወቅ አለበት፡፡

2. ቢሰረዝ፣

3. አንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማሕበር ከላይ በተጠቀሰው ጊዜ ሥለተከፈተው ኤጀንሲውን ሳያሳውቅ ቢቀር በአስተዳደራዊ ደንብ በሚወሰነው ማስረት በገንዘብ ይቀጣል፡፡

**78. ስያሜ የሥራ ቦታ ወይም መተዳደሪያ ደንብ ስለማስወጥ**

1. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማኅበር አስቀድሞ ከኤጀንሲው በጽሁፍ የተሰጠ ፈቃድ ሳያገኝ ስያሜውን ሊለወጥ ወይም ሊያሻሻል አይችልም

**የአቀማመጥ ለውጥ፡-** ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማኅበር የሥራ ቦታውን ወይም መተዳደሪያ ደንቡን ሲለወጥ ወይም ሲያሻሽል ለኤጀንሲው በአንድ ወር ጊዜ ወስጥ ማሳወቅ አለበት፡፡ (ከ ን. ቁጥር 1 የተከፈለ)

2. አንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማሕበር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 በተደነገገው መሠረት ሳይፈጽም ከቀረ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማሕበሩ በደንብ በሚወሰነው መሠረት በገንዘብ ይቀጣል፣

**79. ስያሜ ወይም መተዳደሪያ ደንብ እንዲለወጥ ለማድረግ ኤጀንሲው ያለው ሥልጣን**

1. አ. የለም

2. በአንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማሕበር ላይ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ተፈጻሚ የማሆነው፣

   ሀ. አ. የለም

   ለ. ቢሰረዝ

   ሐ. ቢሰረዝ

   መ. ቢሰረዝ

   ሠ. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማሕበሩ ያቀረበው ስም ለሕግ ወይም ለሞራል ተቃራኒ ሲሆን፣

3. አ. የለም

4. አ. የለም

5. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማሕበሩ መተዳደሪያ ደንብ ካልተለወጠ በስተቀር አግባብነት ባላቸው ህጎች ማስረት ብሐራዊ ጥቅምን የሚጻረር ወይም የሕዝብን ሰላም፣ ደህንነት ወይም የኢትዮጵያን መረጋጋት የሚጎዳ ሆኖ ሲገኝ ኤጀንሲው በማናቸውም ጊዜ

የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማሕበሩ መተዳደሪያ ደንቡን እንዲያሻሽል ሊያዝ ይችላል፡ ፡

6. አንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማሕበር በዚህ ክፍል በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት የማይፈጽም ቢሆን የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማሕበሩ እና የሥራ መሪዎች በወንጀል ሕጉ መሠረት ቅጣት ተጠያቂ ይሆናሉ

## 80. በምልክቶች ስለማጠቀም

1. ማንኛወም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማሕበር ኤጀንሲውን ሳያሳውቅ ማናቸውንም ባንዲራ፣ አርማ ወይም ምልክቶች ማጠቀም አይችልም፣
2. ቢሰረዝ፣
3. አንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተደነገገውን በሚጻረር መንገድ ተጠቅሞ ቢገኝ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማሕበሩ በደንብ በሚወሰነው መሠረት በገንዘብ ይቀጣል፣

## 81. የምስክር ወረቀትን፣ ስያሜና ምልክቶችን በይፋ ስለ ማሳየት

1. አ. የለም
2. ቢሰረዝ፡ ፡
3. አ. የለም

## 82. ሕገ-ወጥ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማሕበራት

1. ማንኛወም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በህግ የተከለከለና እንደ ወንጀል በሚቆጠር ድርጊት ወስጥ ተሰማርቶ ከተገኘ እንደ ህገ ወጥ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ይቆጠራል
2. በማንኛወም ሕገ-ወጥ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማሕበር የማስተዳደር ሥራ ወስጥ እያወቀ የተሳተፈ ማንኛወም ሰው በወንጀል ሕጉ ማሰረት ይቀጣል፣
3. ማንኛወም ሰው እያወቀ በማንኛወም ሕገ-ወጥ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማሕበር ወስጥ አባል የሆነ ወይም እንደ አባል የተሳተፈ ወይም በሕገወጥ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማሕበሩ ስብሰባ ላይ የተገኘ እንደሆነ በወንጀል ሕጉ ማሰረት ይቀጣል፡ ፡
4. ማናቸወም ሰው እያወቀ ለአንድ ሕገ-ወጥ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማሕበር የለገሰ ወይም አስተዋጽኦ ያደረገ ወይም በአባልነት ክፍያ መልክ ወይም በማናቸወም መንገድ ገንዘብ ወይም ንብረት የሰጠ እንደሆነ በአባሪነት ይቀጣል፡ ፡

**83. በቅጥር ግቢ ወስጥ ሕገ-ወጥ ስብሰባ ስለማካሄድ**

ማንኛወም ሰው እያወቀ የእርሱ በሆነ፣ በይዞታው ስር ባለ ወይም በሚቆጣጠረው ቤት፣ ህንፃ ወይም ቦታ የሕገ ወጥ የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር ወይም አባላቱ ስብሰባ እንዲካሄድ የፈቀደ እንደሆነ በወንጀል ሕጉ መሰረት ይቀጣል፡፡

**84. ለሕገ-ወጥ የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር አስተዋጽኦ ወይም እርዳታ ስለማስገኘት**

ቢሰረዝ

**85. የሕገ-ወጥ የበጐ አድራጐት ድርጅትን ወይም ማሕበርን መረጃ ማሰራጨት**

ለአንድ ሕገ-ወጥ የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር ጥቅም እያወቀ ህገ ወጥ መረጃን ያተመ፣ ያሳተመ፣ ለእይታ ያቀረበ፣ የሸጠ፣ ለሽያጭ ያቀረበ፣ በፖስታ ወይም በማናቸወም የኤሌክትሮኒክ ሚዲያ ያስተላለፈ ማንኛወም ሰው በወንጀል ሕጉ መሰረት ይቀጣል፡፡ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘበት ጉዳይ ጋር የተያያዘ ማናቸወም መጽሐፍ፣ በየጊዜው የሚወጣ የሕትመት ወጤት፣ በራሪ ወረቀት፣ ፖስተር፣ ጋዜጣ ደብዳቤ ወይም ሌላ ማናቸወም ሰነድ ወይም ፅሁፍ ይወረሳል፡፡

**86. የፈቃድና ምዝገባ ሰርተፊኬት ስለሚደስ**

1. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት የፈቃድ ሰርተፊኬታቸዉን በየሦስት ዓመቱ ማሳደስ አለባቸው፡፡

**ተጨማሪ፡-** ከላይ በአንቀጽ 86/1/ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት በየዓመቱ የኦዲትና የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ለኤጀንሲው ያቀርባሉ፡፡

2. አ. የለም
3. አ. የለም
4. አ. የለም
5. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ለሶስት ተከታታይ የሂሳብ ዓመታት ከጠቅላላ ገቢው ከ70 በመቶ በላይ የሚሆነወን ለተቋቋመበት ዓላማ ወይም ለፕሮግራም ወይም ለፕሮጀክት ሥራ ካላዋለና በቂ ምክንያት ካላቀረበ የምዝገባ ሰርተፊኬቱ አይታደስም፡፡

**ተጨማሪ፡-** የፕሮግራም ወይም የፕሮጀክት ሥራ ማለት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ እሰራዋለሁ ብሎ ያቀደው ሥራ ሲሆን ይህም ለፕሮግራሙ ወይም ለፕሮጀክቱ ሥራ ሳይሆን ለድርጅቱ ወይም ለማህበሩ የአስተዳደር ሥራ የወጣወን ወጪ አያካትትም

**ተጨማሪ፡** ከዚህ በላይ የተቀመጡት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ኤጀንሲው፣ የዘርፉ አስተዳደሪው እና የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማህበሩ በመመካከር የአስተዳደራዊ ወጪ ከ30 በመቶ በላይ የሚሆንበትን ሁኔታ ይወስናሉ፡፡

6. ከጠቅላላ ገቢው ከ80 በመቶ በላይ ለተቋቋመበት ዓላማ ወይም ለፕሮግራም ወይም ለፕሮጀክት ሥራ ለሚያወም የበጎ አድራጎት ድርጅት መንግሥት የተለያዩ ማበረታቻዎችን ሊያደርግ ይችላል፡፡

ክፍል ሰባት
ስለ የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማሕበራት ሂሣብ እና ሪፖርቶች

**87. የሂሣብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ**

1. አ. የለም
2. አ. የለም
3. የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማሕበራት በማናቸውም ጊዜ የለጋሹን ማንነት በግልጽ የሚያመለክቱ መዝገቦችን መያዝ አለባቸው፡፡
4. አ. የለም
5. አ. የለም

**88. ዓመታዊ የሂሣብ መግለጫ**

አ. የለም

**89. ዓመታዊ የሂሣብ ምርመራ ስለማድረግ**

1. የማንኛወም የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር ሂሣብ በየዓመቱ በተመሰከረለት አዲተር መመርመር አለበት፡፡
2. አ. የለም
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ ቢኖርም ሚኒስትሩ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ማንኛወም ዓይነት የሂሳብ ምርመራ በማንኛወም ጊዜ በወጭ ወይም በወስጥ አዲተር ሊመረመር ይችላል፡፡
4. የበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም የማሕበሩ ሂሣብ ዓመቱ ባለቀ በስድስት ወራት ወስጥ ያለበቂ ምክንያት ካልተመረመረ ኤጀንሲው አዲተር ሾሞ ማስመርመር ይችላል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /4/ መሠረት በኤጀንሲው በተሾመው አዲተር ለተከናወኑ ማናቸወም የኦዲት ሥራዎች ወጭ የሚከፍለው የሚመለከተው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ይሆናል፡፡

**90. አመታዊ ሪፖርት**

1. አ. የለም
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከተው ሪፖርት በሥራ መሪዎቹ ለኤጀንሲው የሂሣብ ዓመቱ ባለቀ በስድስት ወር ጊዜ ወስጥ እንዲሁም ኤጀንሲው በሚፈቅደው ልዩ ምክንያት በሚጠይቀው ጊዜ ወስጥ ማቅረብ አለባቸው፡፡
3. አ. የለም
4. አ. የለም

**91. ዓመታዊ ሪፖርት ለሕዝብ ክፍት ስለማድረግ**

አ. የለም

**92. ለሌሎች ሰዎች ሪፖርት ስለማድረግ**

አ. የለም

**93. የባንክ ሂሣብ ስለማስታወቅ**

1. የበጎ አድራት ድርጅት ወይም የማሕበር መሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የማሕበሩን የባንክ ሂሣብ ከሚፈለገው ዝርዝር ጋር ለኤጄንሲው ከዓመታዊ ሪፖርታቸው ጋር ወይም የባንካቸውን አድራሻ ሲለውጡ ማሳወቅ አለባቸው፡፡
2. አ. የለም

ክፍል ስምንት

የበጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማሕበራትን ስለመቆጣጠር

**94. ምርመራ የማድረግ ሥልጣን**

1. ኤጀንሲው አንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በዚህ አዋጅ ከተቀመጡት ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረን ተግባር ፈጽሟል ለማለት የሚያስችል በማስረጃ የተደገፈ ምክንያታዊ ጥርጣሬ ሲኖር ምርመራ ሊያካሄድ ይችላል፡፡
2. ለእንዲህ ዓይነት ምርመራ ጉዳይ ኤጀንሲው ማናቸውንም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማሕበር ወይም የሥራ መሪ ወይም ጉዳዩ የሚመለከተው ሠራተኛ፡ -
3. አ. የለም
4. ቢሰረዝ
5. በወንጀል ሕጉ ድንጋጌዎች መሠረት ይቀጣል፣

**95. ቢሰረዝ**

**96. ቢሰረዝ**

**97. ቢሰረዝ**

**98. ሀሰተኛ ወይም አሳሳች መረጃ ስለማስጠት**

1. በወንጀል ሕጉ ማስረት ይቀጣል፡፡

2. በወንጀል ሕጉ ማስረት ይቀጣል፡፡

**99. የበጎ አድራጎት ሥራዎችን ስለማስተባበር**

ከላይ በአንቀጽ 16 (በቀድሞው 71) ሥር ቢካተት፡፡

**100. መረጃ ስለመግለጽ**

ሀ. የለም

**101. ቢሰረዝ ( አንቀጽ 86 እና 87 ላይ በማጠቃሉ)**

**102. የውጭ ዜጎችን ስለ መቅጠር**

**ተጨማሪ፡-** በዚህ አንቀጽ ንዑሥ አንቀጽ /1/ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በቅጥር ላይ ያልተመሠረተን የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን ይህ ድንጋጌ አይመለከትም

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከተውን የተላለፈ ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማሕበር በወንጀል ሕጉ ማስረት ይቀጣል፡፡

**103. የንብረት ጥበቃ**

4. ኤጀንሲው ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበርን በተመለከተ በሚያደርገው ክትትል ወይም ምርመራ ተገቢ ያልሆነ የሥራ አመራር ግድፈት ወይም ድርጊት መፈፀሙን በተጨባጭ ሲያረጋግጥ በቅድሚያ ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ራሱን እንዲያርምና እንዲያስተካክል ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡ ሆኖም በትዛዙ ማስረት ያለመጸመን ከተረዳ፡፡

   ሀ. ተገቢ ላልሆነው ሥራ ሃላፊ ወይም ተካፋይ የሆነውን ወይም ለዚህ ድርጊት አስተዋጽኦ ያደረገውን የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም የማሕበሩ ማናቸውንም የሥራ ሐላፊ ከአስተደደር ሥልጣኑ ማገድ፣

   ሐ. ቢሰረዝ

   መ. የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም ማሕበሩን በትክክል ለማስተዳደር ብቁ ናቸው ተብለው የታመነባቸው ተጨማሪ የሥራ መሪዎች እንዲሾሙ እንዲያደርግ ለጠቅላላ ጉባኤው ወይም ለማህበሩ የበላይ አካል ያሳውቃል

   ሠ. ቢሰረዝ

   ረ. ቢሰረዝ፣

**104.የስራ ሜዎችን ስለ ማገድ እና መተካት**

1. ኤጀንሲው አንድን የሥራ ሜ ወይም ወኪል ከሚከተሉት አንዱ ሲሟላ በትዕዛዝ ሊያግድ ይችላል፣

   መ. ቢሰረዝ፣

   ሠ. ቢሰረዝ ፣

2. ኤጀንሲው አንድን የሥራ ሜ ወይም ወኪል ከሚከተሉት አንዱ ሲማላ በጊዚያዊነት ሊመድብ ይችላል፡፡

   ሀ. የድርጅቱ ወይም የማሕበሩ የጠቅላላ ጉባኤ ወይም የበለይ አካል በዚህ አንቀጽ መሠረት ወይም በሌላ አንቀጽ የታገደን ወይም የለቀቀን የሥራ ሜ ለመተካት ካልቻለ፣

   ለ. ቢሰረዝ፣

   ሐ. ቢሰረዝ

   መ. ቢሰረዝ (ድግግሞሽ ለማስቀረት)

**105. የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ስለመሠረዝ**

1. ኤጀንሲው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ወይም ማሕበራትን በሚከተሉት ምክንያቶች ይሰርዛል

   ሀ. ቢሰረዝ፣

   መ. ቢሰረዝ፣

   ረ. የማሕበሩ አባላት ቁጥር በሕግ ከተደነገገው በታች ከሆነና በስድስት ወር ጊዜ ወስጥ ያልተስተካከለ ከሆነ፣

   ሸ. ቢሰረዝ

**106. ፍርድ ቤት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ወይም ማሕበራትን የሚያፈርስበት ሁኔታ**

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በሚከተሉት ምክንያቶች አንድን የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማሕበር ሊያፈርስ ይችላል፡-

   ሀ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 105 መሠረት ኤጀንሲው የሰጠው የማስረዝ ውሳኔ በማንኛውም ምክንያት ካልተሻረ እና የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የማህበሩን መፍረስ ኤጀንሲው ለፍርድ ቤት ካመለከተ፤

**ተጨማሪ፡-** ከ2/3ኛ በላይ የሆኑት የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ አባላት ማህበሩ እንዲፈርስ ጥያቄ ለፍርድ ቤቱ ካቀረቡ

**107. የመፍረስ ወጤት**

1. የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር እንዲፈርስ ወሳኔ ሲሰጥ፣

   ለ. ሂሣብ አጣሪው የበጐ አድራጐት ድርጅቱን ወይም ማሕበሩን እዳዎችና ኃላፊነቶች እንዲሁም የመፍረስ ሂደቱን ለማከናወን የሚያስፈልጉ ወጪዎች ተጠናቀው ከተከፈሉ በኋላ የበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም የማሕበሩ ቀሪ ገንዘብ ወይም ንብረት ካለ ተመሣሣይ ዓላማ ላለው የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ለማንኛወም የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር እንዲተላለፍ በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ማስረት ኤጀንሲው ትዕዛዝ ይሰጣል

2. አ. የለም

## ክፍል ዘጠኝ
## ንብረትን ለተቀራራቢ ዓላማ ማዋል /ሣይ ፕሬ/

**108. ንብረትን ለተቀራራቢ ዓላማ ማዋል የሚፈፀምባቸው ሁኔታዎች**

አ. የለም

**109. የአነስተኛ በጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማሕበራት ልዩ ድንጋጌዎች**

አ. የለም

ክፍል አስር
ሕዝባዊ መዋጮ

**110. ለሕዝባዊ መዋጮ ስለማመልከት**

አ. የለም

**111. በማመልከቻ ላይ መወሰን**

አ. የለም

**112. የሕዝባዊ መዋጮ ፈቃድ የሚያስከለክሉ ምክንያቶች**

አ. የለም

**113. ሕዝባዊ መዋጮ መከልከል ወይም መገደብ**

አ. የለም

ክፍል አስራ አንድ
የገቢ ግብር

**114. ከግብር ነፃ ስለሚደረግና የገቢ ማስገኛ ስራዎች**

አ. የለም

**115. የገቢ ማስገኛ ስራዎች**

አ. የለም

## ክፍል አስራ ሁለት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**116. የወንጀል ድርጊቶች**

1. የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማሕበራት በዚህ ሕግ ከተቀመጡት ወሰኖች ወጪ ማስራት አይፈቀድላቸውም፡፡
2. አ. የለም

**117. ቅጣቶችና የአስተዳደር እርምጃዎች**

አ. የለም

**118. አቤቱታና ይግባኝ**

1. አ. የለም
2. በአንቀጽ 14(1)(ረ) ከተማለከቱት ጉዳዮች በቀር በማንኛውም ኤጀንሲው በሰጠው ወሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ሰው ወሳኔው በተሰጠ በአንድ ወር ወስጥ ለሚኒስትሩ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡ ሚኒስትሩ የሚሰጠው ወሳኔ የመጨረሻ ነው፡፡

**119. ወንጀልን ስለመመርመርና ክስ ስለማቅረብ**

አ. የለም

**120. መዋሐድ**

አ. የለም

**121. መከፋፈል**

አ. የለም

**122. ደንብ የማውጣት ሥልጣን**

አ. የለም

**123. ተፈጻሚነት ስለሚዩኖራቸው ሕጎች**

አ. የለም

**124. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች**

1. አ. የለም
2. ቀደም ሲል ተመዝግበው የነበሩት ሁሉም የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማሕበራት ይህ አዋጅ ተፈጻሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በሦስት ዓመት ወስጥ መመዝገብ አለባቸው፡፡

**125. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

አ. የለም